የሰ/መ/ቁ 43731

ታህሳስ 8 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** ሲ.ጂ.ሲ.ኦቨርሲስ ኮንስትራክሽን ኢትዮጵያ ሊሚትድ - እሌኒ አስራት ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ሰለሞን እንዳለ - አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በሌለሁበት ክርክሩ እንዲሰማ የተሰጠው ትዕዛዝ ተነስቶ ወደክርክሩ እንድገባ ይፈቀድልኝ በማለት አመልካች ያቀረበውን አቤቱታ የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው አመልካች ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተከሣሽ የነበረ ሲሆን፣ መልስ እንዲሰጥ በተጠራበት ቀነቀጠሮ ባለመቅረቡ ክርክሩ እሱ በሌለበት እንዲሰማ ታዟል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ትዕዛዙ እንዲነሳለት እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.72 መሠረት ወደ ክርክሩ እንዲገባ እንዲፈቀድለት ጠይቆአል፡፡ ፍ/ቤቱም ጥያቄውን ከተመለከተ በኋላ፣ አቤቱታው ትዕዛዙ በተሰጠ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ያልቀረበ በመሆኑና የአንድ ወር ጊዜው ያለፈው በበቂ ምክንያት ለመሆኑ የቀረበ ማስረጃ ስለሌለ ትዕዛዙ ሊነሳ አይችልም በማለት ብይን ሰጥቶአል፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ትዕዛዙን አፅንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች የካቲት 16 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ በዚህ ረገድ ግራ ቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክርም አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 13262 ጥቅምት 7 ቀን 2001 ዓ.ም በሰጠው ብይን እንደተመለከተው አመልካች ቀደም ሲል ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ተነስቶለት ወደ ክርክሩ እንዲገባ ባመለከተበት ጊዜ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ አልተሰጠም ነበር፡፡ ከመዝገቡ አጠቃላይ ይዘት መገንዘብ እንደቻልነው አመልካች ተከሣሽ የነበረ ሲሆን፣ በቀረበበት ክስ በጽሑፍ መልስ ሰጥቶ ነበር፡፡ ጉዳዩ ለቃል ክርክር በተቀጠረበት ዕለትም የአመልካቹ ሠራተኛ የሆነ ቀርቦ የነበረ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱ ግን ክርክር ለማቅረብ የሚያስችል የውክልና ሥልጣን የለህም በማለት ክርክሩ አመልካቹ በሌለበት እንዲታይ አዞአል፡፡ ከዚህ በኋላም ነው አመልካች ክርክሩ በሌለበት ይሰማል የሚለው ትዕዛዝ ተነስቶለት ወደክርክሩ እንዲገባ የጠየቀው፡፡ ፍ/ቤቱ በዚህ መልክ የቀረበውን አቤቱታ ውድቅ ያደረገው ጥያቄው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.78(1) መሠረት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አልቀረበም፡፡ በህጉ ከተመለከተው የአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለማቅረብ ያልቻለበት በቂ ምክንያት ያለው ለመሆኑም አላስረዳም የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት ነው፡፡

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ መሠረት የሚመራው የፍትሐብሔር ክስ በቀረበ ጊዜ ክርክሩን ለመስማት ፍ/ቤቱ በያዘው ቀነቀጠሮ ተከራካሪ ወገኖች ይቀርባሉ ተብሎ እንደሚጠበቅ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 69(1) ከተቀመጠው ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች ወይም አንዳቸው ሳይቀርቡ ቢቀሩ ሊወሰዱ ስለሚገባቸው የሥነ-ሥርዓት እርምጃዎች በሚመለከት ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.69 እስከ 78 ድረስ ባሉት ድንጋጌዎች በዝርዝር ተቀምጦአል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ክርክሩ እንዲሰማ ቀነ ቀጠሮ በተያዘበት ዕለት ሳይቀርብ የቀረው አመልካች (ተከሣሽ የነበረው) ነው፡፡ በዚህ ቀነ ቀጠሮ የአመልካች ወኪል ነኝ በማለት የቀረበው ሠራተኛ የተሟላ የውክልና ሥልጣን የለውም በሚል አመልካች

እንዳልቀረበ ተቆጥሮ ክርክሩ አመልካች በሌለበት እንዲታይ የመታዘዙን አግባብነት ወደኋላ የምንመለከተው ይሆናል፡፡ ፍ/ቤቱ ይህን እምነት በመያዙና ክርክሩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 70(ሀ) መሠረት አመልካች በሌለበት እንዲሰማ ትዕዛዝ በመስጠቱ የተነሣ አመልካች ለጉዳዩ የመጨረሻ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ያቀረበው አቤቱታ የሚስተናገደው በምን አግባብ ነው? የሚለውን ነጥብ በቅድሚያ እንመለከታለን፡፡

በመጀመሪያው ቀነቀጠሮ ባለመቅረቡ ምክንያት ክርክሩ በሌለበት እንዲሰማ ትዕዛዝ የተሰጠበት ተከሣሽ በሚቀጥለው ቀነቀጠሮ ቀርቦ በቀዳሚው ቀነቀጠሮ ለመቅረብ ያልቻለው በቂ ሆኖ በሚገመት እክል ምክንያት መሆኑን ያስረዳ እንደሆነና ፍ/ቤቱም ምክንያቱን በቂ አድርጎ የተቀበለው እንደሆነ በቀረበበት ቀን መከላከያውን አቅርቦ እንዲከራከር እንደሚፈቅድለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 72 ተደንግጎአል፡፡ በዚህ ድንጋጌ የተቀመጡት ዋነኞቹ ነጥቦች አቤቱታው የሚቀርበው በሚቀጥለው ቀጠሮ ማለትም ጉዳዩ በውሳኔ ከመቋጨቱ በፊት መሆኑን እና በቀዳሚው ቀነ ቀጠሮ ላለመቅረብ በቂ ሆኖ የሚገመት ምክንያት (እክል) መኖር ናቸው፡፡ ከዚህ ውጪ ድንጋጌው አቤቱታው የሚቀርብበትን ግልጽ የሆነ የጊዜ ገደብ አላስቀመጠም፡፡ በዚህ ይዘቱም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 78(1) ከተደነገገው የሚለይ ነው፡፡ የኋለኛው "ተከሣሽ በሌለበት የተሰጠውን ውሳኔ ስለማንሳት" የሚል ርእስ ያለው ሲሆን፣ የመጀመሪያው ግን "በሚቀጥለው ቀነቀጠሮ ስለመቅረብ" በሚል የተደነገገ ነው፡፡ ከዚህም በሁለቱ ድንጋጌዎች መካከል ያለውን ልዩነት ጉዳዩን በያዘው ፍ/ቤት የመጨረሻ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት እና ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በሚል ሊለይ እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 72 እና 78 መካከል ያለው ልዩነት ይህን ያህል ግልጽ ከሆነ ደግሞ በመጀመሪያው ቀነ ቀጠሮ የቀረ ነገር ግን በሚቀጥለው ቀነ ቀጠሮ የቀረበው ተከሣሽ ጥያቄው ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 78(1) አኳያ የሚታይበት አግባብ የለም፡፡ በመሆኑም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ቁ. 78(1)"ን" መሠረት በማድረግ ጉዳዩን ያየው በአግባቡ አይደለም፡፡

በመቀጠል ያየነው አመልካች በአንድ ወር ውስጥ ቀርቦ ያላመለከተበትን ምክንያት አላስረዳም የሚለውን የፍ/ቤቱ ትችት ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደገለጽነው አመልካች አቤቱታውን ለማቅረብ የቀናትም ይሁን የወራት ገደብ አልተቀመጠለትም፡፡ በመሆኑም እንዲያስረዳ የሚጠበቀው ክርክሩ ሊሰማ በተያዘው ቀነ ቀጠሮ ያልቀረበበትን ምክንያት ነው፡፡ ለክሱ መልስ በተሰጠበት ጊዜ በኋላ በቃል የመከራከር የተሟላ ውክልና የለህም የተባለው ሠራተኛው ከመቅረቡም በላይ፤ መልሱን እራሱ ፈርሞ እንዳቀረበው በክርክሩ ተመልክቶአል፡፡ ጉዳዩን ለመስማት (በቃል) ቀጠሮ በተያዘበት ዕለትም ይኸው ለመከራከር ይችላል ተብሎ ከአመልካች ውክልና የተሰጠው ሠራተኛ የቀረበ በመሆኑ ቢያንስ በኋላ ትዕዛዙ እንዲነሳለት ላቀረበው አቤቱታ አወሳሰን እንደበቂ ምክንያት ተደርጎ ሊወሰድለት ይገባ ነበር፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ አመልካች ያቀረበው በጽሑፍ የተዘጋጀው መልስ ከመዝገቡ የተያያዘ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ከዚህ በመነሳት ወደፊት ያለውን ክርክሩ መሰማት ሲገባው ወደ ውሳኔ ማምራቱ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስናጠቃልለው ፍ/ቤቱ ክርክሩን የመራው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 72 የተቀመጠውን ድንጋጌ በአግባቡ ሳይጠቀም በመሆኑ አፈጻጸሙ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 13262 ጥቅምት 7 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ብይን እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 72956 የካቲት 2 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች ወደ ክርክሩ እንዲገባ በማድረግ ከገባበት ቀን ጀምሮ ወደፊት ያለውን ክርክሩን ከሰማ በኋላ ተገቢውን ይወስን ዘንድ ጉዳዩ ይመለስለት ብለናል፡፡
3. በዚህ ሰበር ችሎት በተደረገው ክርክር ግራ ቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ